ጉባዔ ስምንት::

አ ድንግል አኮ ለዮሴፍ ዘተኀጕርከ. ለተቃርቦ::

ድንግል ሆይ ለዮሴፍ ለተቃርቦ ብእሲ. ወብእሲት የታጨሽ አይደለም አንድም ለዮሴፍ የታጨሽው ለተቃርቦ ብእሲ. ወብእሲት አይደለም::

አላ ከመ ይዕቀብከ. ንጹሐ::

ንጹሕ ሆኖ በትሕትና ሊታዘዝሽ በንጽሕና ሊጠብቅሽ ሊያገለግልሽ ነው እንጂ::

Scanned by CamScanner

እስመ ከማሁ ኮነ።።

ሀብትሽ ሀብተ ንጽሕ ሆኗልና፤ አንድም ዮሴፍ ንጹሕ ሆኖ ይጠብቅ
ዘንድ ነው እንጂ ሀብቱ ክፍሉ ሀብተ ንጽሕና ነውና።። እመቤታችን
የብጽዓት ልጅ ናት በተወለደች በሦስት ዓመቷ ወስደው ሰሊቀ ካህናቱ
ለዘካርያስ ሰጧት፤ ከእናት ከአባቷ ቤት ሦስት ዓመት ከቤተ መቅደስ
ዐሥራ ሁለት ዓመት፤ ዐሥራ አምስት ዓመት ሲሆናት አይሁድ
ለምቀኝነት አያርፉምና ይህች ብላቴና ለአቅመ ሔዋን አደረሰች።። እሷን
ያለ ጎልማሳ ከዚህ አስቀምጠን ቤተ መቅደሳችንን ታረክሰብናለች
እንዲያውም ጠረጠርናት።። ጠይቀህ ያለችውን አድርግላት ከመቅደሳችን
አውጣልን አሉት።። ዘካርያስም ሄዶ ኦ ወለተ እስራኤል እፎ ትፈቅዲ
ትንበሪ ልጄ! እንደምን ሆነሽ ልትኖሪ ትወጃለሽ አላት፤ እመቤታችንም
ፈጸሚተ ፈቃድ ትሑት ናትና ከእግዚአብሔር በታች ያለሽኝ አባት
አንተ ነህ በዚያውም ላይ እናት አባቴ አደራ ያሉ ለአንተ ነው ወደ
እግዚአብሔር አመልክትልኝ አለችው።። ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክት
እግዚአብሔር ሥራውን ያለምክንያት አይሠራምና ከነገደ ይሁዳ ሚስቱ
የሞተችበትን በትር ሰብስበህ በቀዳማይ ሰዓተ ሌሊት ይዘህ ገብተህ
ስትጸልይበት እደር፤ ከዚያ ምልክት አሳይሃለሁ፤ ለዚያ ሰው ስጣት
አለው።። በዚያን ወራት ቢሰበስብ ሺ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አምስት በትር
ሆነ ይህንን በቀዳማይ ሰዓተ ሌሊት ይዞ ገብቶ ሲጸልይበት ቢያድር
ከዮሴፍ በትር ላይ ኦ ዮሴፍ ወልደ ዳዊት ዕቀባ ለማርያም ፍጎርትከ
ዮሴፍ ሆይ እጮኛህ ማርያምን ጠብቃት የሚል ሰማያዊ ሕግ ተጽፎ
ተገኝቷልና።። ርግብም ወርዳ በራሱ ላይ አርፋበታለች፤ ዕጣም ቢጥሉም
ለእሱ ደርሷል እንደ ሦስት ምስክር፤ ልማ በሥሉስ ጥፋ በሥሉስ
እንዲሉ።። በዚያም በዚህም ብሎ ላንተ ደረሰችህ፤ ሱባዔ ገብተን
የሰጠንህን ሱባዔ ገብተን እስክንቀበልህ ድረስ ይዘሃት ሂድ፤ ጠብቃትም
አሉት።። አይሆንልኝም አላቸው፤ ይህማ ናዳብ አብዩድ ባላወቁት
ኃጢአት እንደ ቀሠፋቸው ይቀሥፍህ የለምን ሲሉት በዚህ ጊዜ
ተቀብሎ ወደ ቤቱ ይዟት ሄዷል፤ ዮሴፍ እመቤታችንን ከተቀበለ ወዲህ
ወደ ዓለማዊ ሕይወት አልተመለሰምና ንጽሕና ክፍሉ ነውና አለ።

ወሶበ ርእየ ንጽሕናኪ ለሊሁ እግዚአብሔር አብ።።

እግዚአብሔር አብ ንጽሕናሽን ባወቀ ጊዜ።።

Scanned by CamScanner

ፈነወ ኀቤኪ ብርሃናዊ መልአኮ ዘስሙ ገብርኤል::

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ ወደ አንቺ ሰደደ:: መልአከ ጽልመት አለና ብርሃናዊ አለ፤ ሌላ ተርታ መልአክ አለና ዘስሙ ገብርኤል አለ:: ገብርኤል ማለት አምላክ ወሰብእ እግዚእ ወገብር ማለት ነው:: ብሥራቱን በገብርኤል ያደረገው በምን ምክንያት ነው ቢሉ ሀብተ ብሥራት የተሰጠው ለእርሱ ነውና ጥንቱን አብሣሬ ፅንስ ነውና፤ ቀድሞ አዳምንና ሔዋን ብዙ ተባዙ ምድርን ሙሏት ብሎ የነገራቸው፤ ኋላም በአቤል ሞት ምክንያት አዝነው ተክዘው ከሩካቤ ሥጋ ተለይተው በነበሩበት ሰዓት አቤልን የሚተካ ሴትን እንደሚፀንሱ አብሥሮ ያጽናናቸው እርሱ ነውና:: ከዚያም የነቢያትን የነሶምሶንን የነመጥምቁ ዮሐንስን መወለድ ያበሠረ እርሱ ነውና:: ከዚያም ኢያቄምንና ሐናን እመቤታችንን እንደሚወልዱ ያበሠረ እርሱ ነው፤ ስለዚህ ጥንት በለመደው ግብር ይሁን ብሎ ገብርኤልን ልኮታል፤ ዓቢይ ውእቱ ክብር ዘተውህበ ለከ ኦ ገብርኤል መልአክ ዜናዊ ፍሡሐ ገጽ ሰበከ ለነ ልደተ እግዚእ ዘመጽአ ኀቤነ ወአብሠርካ ለማርያም ድንግል ዘእንበለ ርስሐት ወትቤላ ተፈሥሒ ኦ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ[88] ብሎ ሊቁ ወስዶታል:: አንድም ገብርኤል ጌታን በስም ይመስለዋል ይተባበረዋል ወይም ገብርኤል የሚለው ስም ምሥጢረ ሥጋዌን የሚገልጥ ነው፤ ገብርኤል ማለት አምላክ ወሰብእ፣ እግዚእ ወገብር፣ ፈጣሪ ወፍጡር ማለት ነው፤ ስለዚህ በስሙ ትርጓሜ መሠረት አምላክ ሰው፣ ሰው አምላክ፣ ፍጡር ፈጣሪ፣ ፈጣሪ ፍጡር የሚሆንበትን ምስጢር ያበሥር ዘንድ ገብርኤልን ልኮታል:: አንድም ገብርኤል ማለት ወልደ እግዚአብሔር ማለት ነው ወራብዑሰ ይመስል ገጹ ከመ ገጸ ወልደ እግዚአብሔር እንዲል::[89] አንድም ገብርኤል የጌታ ባለ ወረታ ነው ጌታ መላእክትን ሕያዋን ለባውያን ማእምራን አድርጎ በነገድ መቶ በከተማ አሥር አድርጎ ፈጥሮ በጨለማ ተሠወራቸው:: ስለምን ቢሉ ተመራምረው ይወቁኝ ብሎ፤ አንድም ባሕርይው ረቂቅ እንደሆነ ለማጠየቅ፤ አንድም ካልሹኝ አልገኝም ሲል፤ እነሱም ጊዜው ጨለማ ነበርና አንዱ አንዱን ዳስሦ ባያገኘው አንተ ማነህ ከየት መጣህ

---

[88] ገብርኤል ሆይ ለአንተ የተሰጠህ ክብር ታላቅ ነው ወደ እኛ የመጣ የጌታን ልደቱን ነገርኸን ለድንግል ማርያም ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና ብለህ አበሠርካት:: የረቡዕ ውዳሴ ማርያም

[89] የዐራተኛው መልክም የእግዚአብሔርን ልጅ ይመስላል:: ትንቢተ ዳንኤል ፫ ፡ ፳፭፤

ይለዋል፤ እርሱም እኔስ ያመጣኝን ተፈጥሮዬንም አላውቅም ተውኝ
እየተባበሉ ተፈጥሮአቸውን ብቻ ያደንቁ ጀመር፤ አንድ ሆነው በህብረት
መኑ ፈጠረነ እምአይቱ መጻእነ ለሊነኑ በበርእስነ ተፈጠርነ ወማኮኑ
እምካልዕ[90] ማን ፈጠረን ከወዴት ተገኘን እርስ በርሳችን ተፈጣጠርንን
ሲባባሉ ዲያብሎስ ጥንተ ስመ ሳጥናኤል ይባል ነበር፤ ከሁሉ አልቆ
አግኖ ሊቀ መላእክት ቅሩበ እግዚአብሔር አኃዜ መንጠላዕት አድርጎ
ፈጥሮት ነበርና ወደ ላይ ቢያይ ድምዕ አጣ፤ ወደ ታች ቢያይ እንዲህ
ሲሉ ሰማ ዝም ብዬ አምላክነቱን ለሌላ አሳልፌ እሰጣለሁን? ለምን እኔ
ፈጠርኳችሁ አልላቸውም ብሎ አሰበ። አስቦም አልቀረ እኔ
ፈጠርኳችሁ አለ፤ መላእክትም ማእምራን ናቸውና መልኩም ክንፉም
ንግግሩም እንደ እኛ ነው፤ በምን በልጦ ነው እኔ ፈጠርኳችሁ የሚለን
በማዕረግማ ቢሆን እኛስ ከእኛ በታች ያሉትን ለምን አልፈጠርናቸውም
ነበር፤ ፈጣሪ በሥራው ይታወቃል ፈጥሮ ያሳየን ብለው ፈጥረህ
አሳየን አሉት። እሱም እፈጥራለሁ ብሎ እጁን ወደ እሳት አገባ፤
ፈጀው ዋይ አለ፤ ጌታ በጎቡእ ፈውሶታል። አፋአዊ አምላክ ቢሆን ነው
እንጂ ውሳጣዊ አምላክ ቢሆንማ ምን ስታደርግ ነው ባለኝም ነበር
ስለዚህ የነቢቡንና የገቢሩን እንጂ የነልዮን ነጢአት አያውቀውም ብሎ
አሰበ። ይህን ያሰበበት ልቡን ተሰማው፤ ወአኀድያመ መልአከ ሰላም
ገብርኤል በቃሉ እንዲል።[91] ንቁም በበህላዌነ እስከ ንረክቦ ለአምላክነ
ፈጣሪያችንን እስክናገኘው ድረስ ባለንበት እንጽና ብሎ አረጋግቷቸዋል፤
ድል የተነሣን ጦር አንድ አርበኛ ባጭር ታጥቆ ባለህ እርጋ ብሎ
ጦሩን ያጸና ያረጋጋ እንደ ሆነ ከጌታው ዘንድ ሹመት ሽልማት
እንዲያገኝ፤ ገብርኤልም መላእክትን ጸጥ ባደረጋቸው ጊዜ ሑር
አብሥራ ለወለተ ኢያቄም ብሎ ለብሥራት ባለሟልነት አጭቶት
ነበርና፤ ያ እንደ ደረሰ እንደ ተፈጸመ ለማጠየቅ፤ ዘስሙ ገብርኤል
አለ። አንድም ፈጣሪያችንን እስክናውቅ ድረስ በያለንበት እንጽና ብሎ
አረጋግቷቸው ነበርና ይህን በተናገረበት ቃሉ የጌታችንን ሥጋዌ
ለመናገርና የእመቤታችን አብሣሬ መልአክ ለመሆን አበቃው፤
ወበእንተዝ ደለዎ ለገብርኤል ከመ ይፀር ዜናሃ እንዲል።[92] ጨርሶ

---

[90] መጽሐፈ አክሲማሮስ
[91] መጽሐፈ አክሲማሮስ
[92] ድጓ ዘቅዳስ ያሬድ

Scanned by CamScanner

እንዲያስታቸው ብሎ በስተምሥራቅ በኩል እቤ አነ እግዚአብሔር ለይኩን ብርሃን ብሎ ባሕረ ብርሃን አፍሶላቸዋል፤ ወዲያው ስሙ የተጻፈበት መጽሔተ ብርሃን ሰዶላቸው ያን ይዘው አንድነት ሦስትነት ተገልጦላቸው አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ብለው አመስግነዋል፡፡ እሱን ግን ዛሬ ነገሥታት ጠላታቸውን በእርጥብ ቁርበት ጠቅልለው ገደል እንዲጥሉ ጌታም ዲያብሎስን እንደ እንቧይ አንከብሎ ከኢየሩሳሌም ሰማያዊት አውርዶ በኢዮር ካሉ መላእክት ደርቦታል፤ እስከ ዕለተ ረቡዕ ከዚያ ይሰነብታል፤ በዕለተ ሠሉስ የተፈጠሩ አዝርእትን አትክልትን ዕጸዋትን አይቶ እንዲህ አድርጎ ፍጥረት ማከናወን ለዚህም እንጂ ገዢ አኑሮለት ይሆናል አለ፤ ወደኸው ከሆነ በዚህ ዓለም ላኑርህ? አለው ለእኔማ ደገኛውን ማን ነሥቶኝ አለው፤ በዕለተ ረቡዕ ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት ተፈጠሩ መላእክት ይህን አይተው አመሰገኑ፤ ወአመ ተፈጥሩ ከዋክብትየ ሰብሑኒ መላእክትየ እንዲል መላእክት አመስግነው ዲያብሎስን አመስግን ቢሉት እኔ ከማመስገን ውፁእ ነኝ አላመሰግንም ከወደዳችሁ እኔ አራተኛ አድርጋችሁ አመስግኑኝ አላቸው ወዲያው ሳጥናኤል አያይዞ ዐራት አለቆችን ሾመ፡፡ ከሚካኤልና ከገብርኤል ዘንድ ላካቸው ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ቢሏችሁ ሦስቱ ሰማያት አይመስሏትም እኛም ከጩኸት በቀር ያገኘንው ጥቅም የለም ገዢ ነኝ የሚለውን ወግተን ገለን እጅ እናድርጋት ብሎ ላከ፡፡ ከትዕይንተ ንጉሥ እንደ ገባ ውሻ አድርገው እብድ ውሻ አስመስለው አሳደዷቸው፤ መጥተው ነገሩት ሚካኤል ገብርኤል ቢሏችሁ በእኔ ዘንድ ምን ቁም ነገር አላቸው እንደ ቀለምጺጸ እሳት ናቸው እንጂ ብሎ ሠራዊቱን አሰልፎ ተነሣ፤ እሱ ቁልቁል እየወረደ አቀብ የወጣ ይመስለዋል፤ ጐየ እግዚእ ምስለ አርያሙ ጌታ ሰማዩን ጠቅሎ ሸሸ እያለ አዝምሮ ተመለሰ፤ መላእክትም ይህን ሰምተው ይህ ስሑት ፍጥረት እስከ መቼ ድረስ በፈጣሪው ሲታበይ ይኖራል ብለው ገጠሙት ድል አደረጋቸው፤ ሁለተኛም ቢገጥሙት ድል አደረጋቸው፤ መላእክትም አዝነው ጌታ ሆይ ድል እንድናደርግ ፈቃድህ ባይሆን ነውን ብለው ወደ እግዚአብሔር አመለከቱ፤ ፈቃድስ ፈቃዴ ነውና ድል የሚነሣበትን ግብር እንድታውቁ ላስተምራችሁ ብዬ ነው ብሎ የብርሃን ትእምርተ መስቀል ሰጣቸው እሱን ባየ ጊዜ ድል አድርገውታል፤ በዚህ ጊዜ መላእክት

ከዐራት ተከፍለዋል፤ እኩሌቶቹ ነው ብለዋል፤ እኩሌቶቹ ሀልዎተ እግዚአብሔርን አልመረመሩም፤ እኩሌቶቹ ይሆን አይሆን ብለዋል፡፡ ዲያብሎስ ፈጠረን ያሉትን ከእርሱ ጋራ በእርጥብ ጨለማ እንደ እንቧይ አንከባሎ እንደ ስልቻ ጠቅሎ እንጦርጦስ አውርዷቸዋል፤ ሀልዎተ እግዚአብሔር ያላወቁትን በአየር በትኗቸዋል፤ ይሆን አይሆን ያሉትን በዚህ ዓለም እንደ ጨው በትኗቸዋል፡፡ እግዚአብሔር ለመላእክት ፍጥረቶቹ ናቸውና የብርሃን መጎናጸፊያ አጎናጸፋቸው፡፡ ተገዢዎቹ ናቸውና የብርሃን ዝናር አስታጠቃቸው፡፡ ሠራዊቶቹ ናቸውና ማኅተመ መስቀል የሆነ የብርሃን ዘንግ አስያዛቸው፡፡ መውጣት መውረድ አለባቸውና የብርሃን ጫማ አጫማቸው፡፡ እኔን ለማየት በፈቀዳችሁ ጊዜ እኔን ማየት አይቻላችሁም ሲል የብርሃን መነጽር መስታዋት አስያዛቸው፡፡ የጸጋ መንግሥት አነግሣችኋለሁ የጸጋ ክብር አከብራችኋለሁ ሲል የብርሃን አክሊል ደፋላቸው፡፡

ዲብሎስ ማለት ውዑይ ፆፍ፤ ሠራሪ ፈታዊ አምላክና በሐሰት መስተዋድይ በዓመፃ የሐሰት አባት ማለት ነው፡፡

ወይቤለኪ፡፡

እሱም መጥቶ እንዲህ አለሽ፡፡

መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ፡፡

መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል፡፡

ወኀይለ ልዑል ይጼልለኪ፡፡

ኀይለ ልዑል ወልድ ከሦስቱ ግብራት ይከለክልሻል፤ ከዘርእ ከሩካቤ ከሰስሎተ ድንግልና፡፡ ውእቱሰ ንጹሕ እምነ ሠለስቱ ግብራት ዘውእቶሙ ዘርእ ወሩካቤ ወሰስሎተ ድንግልና እለ ሥሩዓን በእጓለ እመሕያው ወእሙራን ቦሙ እንዲል፡፡ አንድም መንፈስ ቅዱስ ኀደረ ላዕሌኪ፤ መንፈስ ቅዱስ ቢያድርብሽ ወኀይለ ልዑል ይጼልለኪ ኀይለ ልዑል ወልድ ሥጋሽን ቢዋሐድ፤ ኀይለ ልዑል መንፈስ ቅዱስ ይላል ኀይለ ልዑል መንፈስ ቅዱስ ቢያድርብሽ፡፡

መጽአ ኀቤኪ ቃል እንዘ ኢይትፈለጥ እምሕፅነ አቡሁ፡፡

አካላዊ ቃል ከአባቱ ዕሪና ሳይለይ ሰው ይሆን ዘንድ ወደ አንቺ መጣ፤ ወኢፈለሰ መካን ውስተ መካን ከመ መላእክት እንዲል፡፡

ወንስኤ እንዘ ኢይትጋባእ።

ከምልአቱ ከባሕርዩ ሳይወሰን በማኅፀንሽ መሰንሸው ሰልማዱ ሰው ሲሆነስ ከአባት አብራክ ከእናት ማኅፀን ተከፍሎ ነውና ይህ ሳይሆን ወነሸው።

ተዐቂረ ውስተ ማኅፀንኪ እንዘ ኢየሐፅፅ በላዕሉ።

በአንድነቱ ሕጸጽ ሳይኖርበት ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነሥቶ በማኅፀንሽ ተወሰነ።

ወኢይትዋሰክ በታሕቱ።

ሥጋ ሁለተኛ ሳይሆነው፤ አንድም እንዘ ኢየሐጽጽ በላዕሉ በሦስትነቱ ርባዔ ሳይኖርበት ወኢይትዋሰክ በታሕቱ፤ በአንድነቱ ምንታዌ ሳይኖርበት፤ አንድም እንዘ ኢየሐጽጽ በላዕሉ ሥጋ ለቃል ምልአተ አካል ምልአተ ክብር ሳይሆን። ወኢይትዋሰክ በታሕቱ፤ ቃል ለሥጋ ሕፀፀ አካል ሕፀፀ ክብር ሳይሆነው፤ አንድም እንዘ ኢየሐፅፅ በላዕሉ ቃል ለሥጋ ሁለተኛ ሳይሆነው፤ ወኢይትዋሰክ በታሕቱ ሥጋ ለመለኮት ዐራተኛ ሳይሆነው በማኅፀንሽ ተወሰነ፤

ኀደረ ውስተ ከርሥኪ እሳተ መለኮት ዘአልቦቱ ጥያቄ ወኢመጠን።

ልክ መጠን የሌለው የማይመረመር እሳተ መለኮት ባሕርየ መለኮት በማኅፀንሽ ተወሰነ። የዕንሷን ነገር ከዚህ ይናገሩታል እመቤታችን ከቤተ ዮሴፍ ሳለች ከዕለታት አንድ ቀን ምንስ ቢሆን ሴት አይደለሁም ብላ ባጭር ታጥቃ ገንቦዋን ነጥቃ ውኃ ልትቀዳ ወደ ወንዝ ሄደች። ወመጽአ ጽሙዕ ክልብ ወሰደዳሁ ውእቶን አንስት ይላል የተጠማ ውሻ መጣ ሴቶች አባረው ደብድበው ሰደዱት፤ ምነው አታጠጡትም እሱስ የእግዚአብሔር ፍጡር አይደለም? አሉቻቸው። አንቺ ሥራ ፈቲቱ አጠፈኪው አንጂ እኛስ ለባሎቻችን ለልጆቻችን እናስባለን፤ በዚያውስ ላይ እንዲህ ያለውን ርኅራኄ ከወደዔት አገኘሽው አምላክ ይወለዳል የሚባለው ካንቺ ይሆን ብለው ተዘባበቱባት። በዚያን ወራት ማርያም ከምትባል አምላክ ይወለዳል እየተባለ ትንቢት ይነገር ነበርና። እመቤታችንም ዕቃዋን እንዳያረክስባት የወርቅ ጫማ ነበራትና ከገንቦዋ ቀድታ አጠጥታዋለች። ርኅርኂተ ልብ ያለኛት አንዱ ይህ ነው። ሴሰይኒ ማርያም ለጸማድኪ ሐሳብ ኀበስተ አእምሮ ሠናየ ወወይነ ጥበብ እመኒ ፈድፋደ ኀጢአትየ እምሕዝብ ተዘከሪ እግዝእትየ

በርኅራኄኪ ዕፁብ ከመ አስተይኪዮ ማየ ለጽሙዕ ከልብ[93] እንዳለ ደፊሲ፡፡ ናሁ አንተጊ ግምኤኪ ወዐዘቅቱኒ ዕሙቅ ውእቱ እንዲል ማድጋሽን አጎደልሺው፤ ቀድቼ እሞለዋለሁ እንዳትዪ ውኃው የጉድጓድ ውኃ ነው መቅጃ የለሽ አሏት፤ አኮ ማይ ዘይወፅእ እምታሕቱ አላ እምላዕሉ ውኃ የሚገኝ ከላይ ነው እንጂ ከወደታች ነውን ይህን ውኃ የፈጠረ ይሰጠኛል አለቻቸው በተአምራት ሞልቶላታል፡፡ አጠጥታው ስትሄድ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል በመንገድ ቆይቶ ስለትሕትና ትፀንሲ ትወልዲ አላት ቀድሞ እናቴ ሔዋንን አባቴን አዳምን ያሳተ እኩይ ሰይጣን ደግሞ ዛሬ እኔንም ሊያስተኝ ነው ብላ መልስ ሳትመልስለት ዝም ብላው ትሄዳለች፤ ከቤቷ ሄዳ ገንቧን አኑራ ተቀምጣ ሳለ ትፀንሲ ትወልዲ አላት ይህ ነገር ደጋገመኝ ደግ ነገር ነው መሰለኝ ከቤተ እግዚአብሔር ሄጀ ልረዳው ብላ ከቤተ እግዚአብሔር ሄዳ በወርቅ ወንበር ተቀምጣ ወእንዘ ትፈትል ወርቀ ወሜላተ አስተርአያ ገብርኤል ግብተ ይላል ወርቁን ከሐር ሐሩን ከወርቅ እያዋሐደች እያስማማች ስትፈትል ቅዱስ ገብርኤል በሽማግሌ አምሳል ብታያት አንደበቱ የሳሳ ልቡናው የረሳ ምን ይዘበዝበኛል ብላ ነገሬን አትቀበለኝም፤ ጎልማሳ መስዬ ብታያት ትፈራኝ ይሆናል ብሎ ሽበት ጣል ጣል ያደረገበት ማዕከላዊ ሰው መስሎ አንዴ እየፈታ አንዴ እየታጠቀ እየሰገደ ጸጋን የተመላሽ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ ደስታ ይገባሻል፤ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ አላት፤ እመቤታችንም የመፅነስንና የመውለድን ነገር ስንኳን ታደርገው አታስበውም ነበርና ከቃሉ የተነሣ ደነገጠች፡፡ እመቤታችንም ለፍጡር እንዲህ ያለ ምሰጋና ይገባዋልን፤ እምአይቴ ረከብከ ዘከመዝ ብሥራተ ዘእንበለ ዘርእ እምድር እትወተ ወዘእንበለ ምት እምድንግል ፅንሰተ ምድር ደግሞስ እንዲህ ዓይነቱን ብሥራት ከወዴት አገኘኸው ምድር ያለዘር ታበቅል ዘንድ ሴት ያለ ወንድ ትፀንስ ዘንድ እንደምን ይቻላል አለችው፤ እመቤታችን ይህን ማለቷ ተጠራጥራ አይደለም እኔ አላደርገውም ብላ ቁርጥ አድርጋ ስትናገር ነው እንጂ፡፡ ይህንም ሊቁ ዘንተ ትቤ ድንግል በእንተ ዘኢዐርገ ኅሊና እጓለ እመሕያው ውስተ ልባ ብሎ ወስዶታል፡፡

---

93 ማርያም ሆይ ለኔ ለባርያሽ ያማረ የዕውቀት ምግብንና የጥበብን ወይን መግቢኝ ኃጢአቴ ከሕዝብ ሁሉ ቢበዛም እመቤቴ ድንቅ በሆነው በርኅራኄሽ አስቢኝ ለተጠማው ውሻ ራርተሽ ውኃን እንዳጠጣሽው፡፡ ሰዓታት አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ

የአንቺ ዕንስ እንደ ሌሎች ሴቶች በዘር በሩካቤ አይደለም መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል ወኀይለ ልዑል ይጼልለኪ ኀይለ ልዑል ወልድ ከሦስቱ ግብራት ይከለክልሻል ከዘርእ ከሩካቤ ከሰስሎተ ድንግልና፡፡ ውእቱሰ ንጹሕ እምነ ሠለስቱ ግብራት ዘውእቶሙ ዘርእ ወሩካቤ ወሰስሎተ ድንግልና እለ ሥሩዓን በእጓለ እመሕያው ወእሙራን ቦሙ እንዲል፡፡ አንድም መንፈስ ቅዱስ ኀደረ ላዕሌኪ፤ መንፈስ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ ቢያድርብሽ፤ ወኀይለ ልዑል ይጼልለኪ ኀይለ ልዑል ወልድ ሥጋሽን ቢዋሐድ ካንቺ የሚወለደው ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ተብለው ከሚመሰገኑት ከሦስቱ ቅዱስ አንዱ ቅዱስ ነው፡፡ አንድም ካንቺ የሚወለደው የአብ ክብሩን ጸጋውን ወርሶ በቤተ ያዕቆብ ዘለዓለም ነግሦ የሚኖር፤ ለመንግሥቱ ጥንትና ፍጻሜ የሌለው፤ ክቡር ወሀቤ ሀብታት ወሀቤ በረከት ነው አላት፡፡ እፎ ይከውነኒ ብላው ነበርና በምሳሌ ያስረዳት ዘንድ ፈልጎ እንዲህ አላት እመቤቴ ሆይ! ወናሁ ኤልሳቤጥኒ እንተ እምአዝማድኪ ይእቲኒ ፀንሰት ወረከበት ወልደ በልሕቃቲሃ ወበርስሐቲሃ ሩቅ አይደለች ቅርብሽ ባዕድ አይደለች ዘመድሽ የምትሆን ኤልሳቤጥ ደሟ ከቀረ ማኅፀኗ ካረረ፤ የዘካርያስም ጀርባው ካረረ ዘሩ ከተመተረ በኋላ ከፀነሰች ስድስተኛ ወር ሆኗታል፤ አንቺ የዐሥራ አምስት ዓመት ቆንጆ ብላቴና ስትሆኚ አልፀንስም አልወልድም ትያለሽን አላት፡፡ እመቤታችንም ለኤልሳቤጥ ምንም ቢሸመግል ዘካርያስ ምክንያት አላት፤ ለእኔ ምን ምክንያት አለኝ? አለችው፤ አሁን እንዲህ ማለቷ እንደ ዘካርያስ ተጠራጥራ እንደ ኒቆዲሞስ ተከራክራ አይደለም፤ ተደርጎ የማይታወቅ ነገር ስለሆነ እንድረዳው ብላ ነው እንጂ፤ ቅዱስ ገብርኤልም የፈራ አጥር ያጥራል፤ ነገር የፈራ ቀን ይቀጥራል እንዲሉ እመቤቴ ሆይ! እስመ አልቦ ነገር ዘይሰአኖ ለእግዚአብሔር ሙቀት ልምላሜ ከተለየ በኋላ ልጅ እንዲወልዱ ማድረግ ለእግዚአብሔር እንደማይሳነው ሁሉ አንቺንስ በኅቱም ድንግልና ፀንሰሽ በኅቱም ድንግልና እንድትወልጂ ቢያደርግሽ ለእግዚአብሔር ይሳነዋል ትያለሽን? ብሎ ነገሯን ወሰነባት፡፡ እመቤታችንም ነየ አመተ እግዚአብሔር ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ ይሳነዋልማ ብል ክህደት ይሆንብኝ የለምን ብላ እነሆ የእግዚአብሔር ገረዱ አገልጋዩ በፊቱ አለሁለት፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ እንዳልክ ይደረግልኝ አለችው፡፡ ይህን ቃሏን ምክንያት አድርጎ ከሦስቱ ቅዱስ

እንዱ ቅዱስ ዋሕድ ታለ እግዚአብሔር በግብረ መንፈስ ቅዱስ ድን ጊዜ
በማህፀኗ ተቀረፀ።
አርቱዕ እክ ናስተማስሎ በአሳት ምድራዊ።
በምድራዊ አሳት ልንመስለው አይገባም።
አሳትስ ቦቱ መጠን ወቦቱ አክል።
ለአሳት ልክ መጠን አካል አለው። መጠኑ በአሳተ ባቢሎን ታውቋል፣
ነት ወተለዐለ ነበልባሉ አርብዐ ወተስዓቱ በአመት እንዲል። አካሉ
እንደ እንጨቱ መደነስ እንደ እንጨቱ መቅጠን ነው።
ወመለኮትስ ኢይትከሀል ይትበሀል ዘንተ የአክል ወዘንተ ይመስል።
መለኮትስ አካሉ ይህን ያህላል መልኩም ይህን ይመስላል ሊባል
አይችልም።
አኮ ዘቦቱ ለመለኮት ክበብ ከመ ወሐይ ወወርኅ።
ለመለኮት እንደ ወሐይ እንደ ጨረቃ የተወሰነ ክበብ አለው አይባልም
የለውምም።
ወአትም ከመ ሰብእ።
እንደ ሰው ሦስት ክንድ ከስንዝር ቁመት ያለው አይደለም የለውምም።
አላ መንክር ውእቱ።
ዕፁብ ድንቅ ነው እንጂ።
ወንውር ዲበ አርያመ ኀበ ኢይበጽሉ ኅሊና ሰብእ ወኢዘመላእክት አእምሮ።
የሰውና የመላእክት አእምሮ መርምሮ የማያገኘው በላይ በአርያም
በልዕልና ያለ ነው እንጂ። ከኻያ ሁለቱ ሥነ ፍጥረት አእምሮ ለብዎ
ያላቸው ሰውና መላእክትን ነውና። አንድም ከእንስሳት ከአራዊት ለይቶ
አዋቂ ለባዊ አድርጎ የፈጠረው ሰውና መላእክትን ነውና።
አኮ ዘቦቱ ለመለኮት ግድም ወኑኅ ላዕል ወታሕት።
ለመለኮት ወርድ ቁመት ላይ ታች ያለው አይደለም የለውምም።
የማን ወፀጋም።
ለመለኮት ቀኝ ግራ ያለው አይደለም የለውምም።

አላ ምሉእ ውእቱ እንተ በኵሉሄ ወበኵሉ፡፡

በዐራቱ ማዕዘን ምሉእ ነው እንጂ፡፡

አኮ ዘቦቱ ለመለኮት ምስፉሕ ወምስትጉቡእ፡፡

ለመለኮት የሚሮጥበት ሰፊ ሜዳ የሚሾልክበት ጠባብ ቀዳዳ፣ ወምስትጉቡእ የሚወርድበት ቁልቁለት የሚወጣበት አቀበት አለው አይባልም የለውምም፡፡ አንድም ምስፉሕ ለመለኮት የሚገኝበት ሰፊ አዳራሽ፤ ወምስትጉቡእ የሚሠወርበት ጠባብ ዕልፍኝ አለው አይባልም የለውምም፡፡ አንድም ምስፉሕ ለመለኮት የሚመክተው ጋሻ የሚገባበት ዋሻ አለው አይባልም የለውምም፤ ወምስትጉቡእ ለመለኮት የሚጨብጠው ቅጠል የሚጋርደው ገደል አለው አይባልም የለውምም፡፡ አንድም ምስፉሕ ለመለኮት እንደ ራስ፣ እንደ ደጃዝማች፣ እንደ ቢትወደድ ያለ ሰፊ ግዛት ወምስትጉቡእ እንደ ቀኛዝማች እንደ ግራዝማች ያለ ጠባብ ግዛት ያለው አይደልም፡፡ አንድም ምስፉሕ ሰፊ ርስት ጉልት ወምስትጉቡእ የተወሰነ ርስት ጉልት አለው አይባልም የለውምም፡፡ ባለጉልት እጀ ክት ዳሩ እሳት መሐሉ ገነት እንዲሉ፡፡

አላ ውስተ ኵሉ በሐውርት መለኮቱ፡፡

አገዛዙ በአራቱ ማዕዘን ምሉእ ነው እንጂ፡፡ አንድም ጌትነቱ ከደረሰበት ሁሉ መልቶ ይኖራል እንጂ፡፡

አኮ ዘቦቱ ለመለኮት ዘበላዕሉ ጠፈር ወዘበታሕቱ መሠረት፡፡

ለመለኮት በላይ ጠፈር በታች መሠረት አለው አይባልም የለውምም፡፡ አንድም በላይ መነሻ መዳረሻ በታች መጨረሻ አለው አይባልም የለውምም፡፡

አላ ጠፈር ውእቱ ወመሠረት ውእቱ፡፡

ጠፈሩም መሠረቱም እሱ ነው እንጂ፡፡ አንድም መጨረሻውም መዳረሻውም እሱ ነው እንጂ፤ ከላይ ጽርሐ አርያም ከታች በርባሮስ አይወስነውም፤ ጽርሐ አርያምን በርባሮስንም እሱ ይወስነዋል እንጂ ይጼዐን ቀመረ ወይነብር ጠፈረ አኃዜ ዓለም በእራኑ እንዲል፡፡

አኮ ዘቦቱ ለመለኮት ምድናን ወአትሕቶ ርእስ ከመ ይንሣእ እምድር ዘኮነ ውስቴቱ፡፡

ለመለኮት ከምድር የወደቀውን ለማንሣት አንገት ቀለስ ወገብ ጎንበስ ማድረግ የለበትም፡፡

ወብሩህ ውእቱ፡፡

በጎላ በተረዳ፤ አንድም ንጹሕ ከተድኅሮ ከተፈልጦ፤ ወጽሩይ ካለመመለክ ካለመሰገድ፤ ወብሩህ ውእቱ ከአፍአዊ ልብስ ንጹሕ ነው፡፡

Scanned by CamScanner